# ግጥም ለዓይነቱ ፤

ነኝ የተቀባሁ፣
እዩት አንገቴን፣
ያን ሁሉ ያየሁ፣
ዕወቁልኝ ኢትዮጵያዊነቴን።

እኔም ነኝ ጦቢያዊ፣
ስሜ ይመስክር ቀለሜ፣
የታላቁ ሕዝብ ወገናዊ፣
ዘውገ ነውና ስሜ።

እኔም አለኝ፣
ወንድም እህት፣
ኢትዮጵያዊ ነኝ፣
እስካለሁ ኣስከሞት።

ዘውገ ማለት ወገን፣
በአማርኛው ዜጋ፣
ጠብቁ ስሟን፣ ክብሯን
ይጥፋ እሷን የሚወጋ።

የትናንቱ ፍጡር፣
የዛሪው አለቃ፣
ያቁም አይወዳደር፣
ጥጋቡ ያብቃ፣
ያቁም ፉክክር፣
ከኢትዮጵያ ጋር።

ሰላምን ይረዳ፣
ጥፋት አይረሳ፣
ለዓለም አይሁን ፍዳ፣
ዳግም አይድረስ አይነሳ።

ወገኔ አንበሳ፣
የለበትም ዕዳ፣
ደግሞ አይነሳ፣
ተራራ ሸለቆ ሜዳ፣
ሳይጥል ሳያወርድ ሳያነሳ፣
አይመለስም ምሷል በካሳ።

ዘውገ ፋንታ